# የግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ፡ም አራተኛ ዓመት መታሰቢያ "የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ቀን" በቶሮንቶ ተከበረ

በግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ/ም ጠቅላላ ምርጫ 26 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ወጥቶ የወያኔን ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ አሽቀንጥሮ የጣለበት አራተኛ ዓመት መታሰቢያ እሑድ ሜይ 17 ቀን 2009 በቶሮንቶ፡ ካናዳ ተከብሮ ውሏል።





በዚህ የቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ ድርጅት በካናዳ ባዘጋጀው የአራተኛ ዓመት የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ቀን ጥሪውን አክብረው ብዙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የተገኙ ሲሆን የዕለቱ ፕሮግራም እስኪጀመር ድረስ የተለያዩ የቪዲዮ ትዕይንቶች ታይተዋል።



ቀጥሎም የዕለቱን ፕሮግራም የቦርዱ ፀሐፊ በስብሰባው የተገኙትን እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉና ፕሮግራሙን ካስተዋወቁ በኋላ ስብሰባውን የቶሮንቶው ድጋፍ ድርጅት ሊቀመንበር ንግግር አሰምተዋል፡፡ ንግግራቸውን የጀመሩት በትግሉ ክቡር ሕይወታቸውን በደማቸው ለከፈሉት፣ ለታሰሩት፣ ለተደበደቡት፣ ለተሰቃዩትና ለተሰደዱት ኢትዮጵያውያን የህሊና ጸሎት በማድረግ ሲሆን፤ ለጀግኖች ሰማዕቶቻችን እስከ ፕሮግራሙ መጨረሻ ድረስ የመታሰቢያ ሻማ ሲበራ ቆይቷል፡፡

ሊቀመንበሩም በንግግራቸው ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ፡ም የኢትዮጵያ ሕዝብ ስላስመዘገበው ድል ሰፊና የጠለq ገለጻ ከማድረጋቸውም በላይ ወደፊትም ሌላ ድል እንደሚገኝና ሕዝብም የመረጠው ፓርቲ የመንግሥት ሥልጣን እንደሚረከብ ያላቸውን ጽኑ እምነት ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ይህ ድል እንዲገኝ በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚጠበቅበትን እርዳታና ድጋፍ ማድረግ አማራጭ የሌለው ግዴታ መሆኑን አጥብቀው አሳስበዋል፡፡

ቀጥሎም የተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን ኮሚቴ በቶሮንቶ ስለ ግንቦት ሰባት ያዘጋጀውን መልዕክት አስተላልፏል፡፡ መልዕክቱም በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በውስጥ የሚካሄደውን የዲሞክራሲ ትግል ያለመሰልቸት አስፈላጊውን ሁሉ እርዳታና ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው ነበር፡፡ ባጠቃላይ በህብረትና በጋራ መስራት የትላንትም የዛሬም የወደፊትም መፈክራችን ስለሆነ ወደዚያው ጎዳና መጓዝ አለብን በማለት ተደምድሟል፡፡

ቀጥሎም የግጥምና የውይይት መድረክ ተካሂዷል፡፡ በውይይቱ መድረክ ተሳታፊዎች በጋራ መታገልን በሚመለከት በጥራትና በማያዳግም መልኩ ሌላ የግንቦቱ 7 ዓይነት ድል ማስመዝገብ አለብን የሚሉ አስተያየቶች፣ ጥያቄዎችና ምክሮች፣ ትንታኔዎች ተሰጥተዋል፡፡

በመጨረሻም ክቡር ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል የመኢአድ ፕሬዚዳንት በስብሰባው ለተገኙት በስልክ አገር ቤት ስለሚደረገው እንቅስቃሴና ወደፊት ስለሚካሄደው ሰላማዊ ትግል ሰፊ ገለፃ ከማድረጋቸውም በላይ፤ ሁሉም የሚችለውን የትግል አስተዋፅኦ እንዲያደርግ አሳስበዋል፡፡

በመልዕክታቸውም መኢአድ አገር ቤት ከሕዝቡ ጋር በመሆን ከፍተኛ ስራ እየሰራ መሆኑን፣ ስለወጣቶች መደራጀት፣ በዋናው ጽህፈት ቤት በተለያዩ እርዕሶች ላይ ስለሚሰጠው ትምህርት፣ በየገጠሩ የዞንና የወረዳ ጽህፈት ቤቶች መከፈት ጉዳይ ግልፅ በሆነና በሚያበረታታ መንፈስ ገልጸዋል፡፡ ስለሚያጋጥማቸውም ችግር የገዢው ፓርቲ ሹማምንት በመኢአድ አባሎችና

EthioLion.Com

ደጋፊዎች ላይ ስለሚያደርሱባቸው እስራት፣ መንገላታትና ስቃይ ጠቅሰው በተጨማሪ ደግሞ የሪሶርስ እጥረት በስራቸው ላይ ከፍተኛ ጫና ያስከተለ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ንግግራቸውንና ገለጻቸውን ሲጨርሱም ጥያቄ ያላቸው ሰዎች ካሉ ማቅረብ እንደሚችሉ ስላሳወቁ ከቤቱ የተለያዩ ጥያቄዎችና የድጋፍ አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡ ለመጥቀስም ያህል በገጠር እንዴት መንቀሳቀስ ትችላላችሁ? ምን ያህልስ ዘልቃችሁ ማደራጀት ትችለላችሁ? በሚቀጥለው ምርጫ 7ቱ ያስቀመጣችኋቸው ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው ትላላችሁ ወይ? በውጭ አገር ስላለው የድጋፍ ድርጅቶች ችግር ጉዳይ ለምን መፍትሔ አትሰጡም? ሌሎችም ተመሳሳይ ጥያቄዎች ቀርበው ነበር፡፡ ክቡር ኢንጂነር ሃይሉም በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል በሁሉም ዞኖችና በከፊል ወረዳዎች መደራጀታቸው ከ63 በላይ ፅህፈት ቤቶች እንዳሉ ከትግራይ ጀምሮ እስከ ሲዳሞ ከወለጋ እስከ ሀረርጌ ድረስ በዞንና በወረዳ ደረጃ ያደራጁ መሆኑን ከዚህ በፊት ከጋምቤላና ኡጋዴን በቀር በሁሉም ክፍለሀገር ያደራጁ በመሆኑ የአሁኑ አስቸጋሪ አለመሆኑ ሲገልጹ ለደህንነት ሲባልና በአቅም ምክንያት በአንዳንድ ቦታዎች የታቀደውን ያህል ለመሄድ አለመቻላቸውን ገልፀዋል፡፡ ስለሚቀጥለው ምርጫ ዝግጅት ምርጫው ነፃና ትክክለኛ እንዲሆን ከተፈለገ ቅድመ ምርጫ ጥያቄዎች መሟላት ይኖርባቸዋል ያ ከሆነ ደግሞ የሕዝቡን ምርጫና ፍላጎት ስለምናውቅ ማሸነፋችን ምንም ጥርጥር የለውም እንደው ሙሉ ለሙሉ እንኳን ባይሟሉም መሰረታዊ ነገሮች ከተሟሉ ሕዝብ እንደሚያሸንፍ እርግጠኛ ነን ብለዋል፡፡ በመጨረሻም በውጭ ያላችሁ ትግሉን ማገዝ ከፈለጋችሁ የሕዝቡን አደራ ለእናንተ እሰጣለሁ አደራ ከማለት ውጭ ሌላ የምለው ነገር የለምና አደራውን ተቀበሉ በማለት መልዕክታቸውን ደምድመዋል፡፡ አክለውም ምነው በሌላም ቦታ ያለው ደጋፊ እንደቶሮንቶ እንዳላችሁት ቢሆኑ፡ እናንተን የያዘ መልካም መንፈስ ለእነርሱም ቢጋባ በማለት መልካም አስተያየታቸውንና ምስጋናቸውን አቅርበው ተሰብሰቢውም እጅግ በጋለና በሞቀ መንፈስ በጭብጨባ ተሰናብቷቸዋል፡፡

በመጨረሻም አንድ ግጥም ተሰምቶ ስብሰባው በጋለ ስሜት ተጠናቋል፡፡ በሚቀጥለው ዓመት ደግሞ የመታሰቢያ ሳይሆን የድል በዓል የሚከበርበት ቀን እንደሚሆን ፅህፈት ቤቱ ያምናል፡፡